የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES' REPRESENTATIVES OF THE FDRE

# በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት
# የውሃ፣ መስኖ፣ ቆላማ አካባቢና
# አካባቢ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ
# የ2014 በጀት ዓመት የተከለሰ ዕቅድ

ህዳር 2014 ዓ.ም

# ማ ው ጫ

ገጽ

**ክፍል አንድ** ........ 1
1. *መግቢያ* ........ 1
**1.1 የውሃ፣ መስኖ፣ ቆላማ አካባቢና አካባቢ ጥበቃ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት** ........ 2
1.2 የቋሚ ኮሚቴው ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ እሴቶች ........ 4
ሀ/ ራዕይ /Vision/ ........ 4
ለ/ ተልዕኮ /Mission/ ........ 4
ሐ/ ዕሴቶች / Values / ........ 4
1.3 የእቅዱ ዋና ዓላማ ........ 4
1.4 የዕቅዱ ዝርዝር ዓላማዎች ........ 5
**ክፍል ሁለት** ........ 5
**2. የዕቅዱ መነሻ ሁኔታዎች ግምገማ** ........ 5
**2.1 የተፈጥሮ ሀብት መስኖና ኢነርጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የ2013 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም እንደ መነሻ** ........ 5
**2.2 አቅም ግንባታ ተግባራት አፈጻጸም** ........ 5
**2.3 የሕግ ማውጣት ተግባራት አፈጻጸም** ........ 6
**2.4 የክትትልና ቁጥጥር ተግባራት አፈጻጸም** ........ 6
2.5 የባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮች አፈጻጸም ........ 7
2.6 የተፈጥሮ ሀብት መስኖና ኢነርጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የ2013 በጀት ዓመት አፈፃፀም ጥንካሬዎችና ድክመቶች ........ 7
ሀ/ በቋሚ ኮሚቴው የነበሩ ጥንካሬዎች ........ 7
ለ/ በቋሚ ኮሚቴው የነበሩ ድክመቶች ........ 8
2.7 ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች፤ ........ 8
ሀ/ ያጋጠሙ ችግሮች ........ 8
ለ/ የተወሰዱ መፍትሂዎች ........ 8
ክፍል ሶስት ........ 9
3. የውሃ፣ መስኖ፣ ቆላማ አካባቢና አካባቢ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የ2014 በጀት ዓመት መሪ ዕቅድ ........ 9
3.1 የቋሚ ኮሚቴው ቁልፍ ተግባር ........ 9
3.2 የዝግጅት ምዕራፍ ........ 9
የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት ........ 9
3.3 የተግባር ምዕራፍ ........ 10

አቅም ግንባታ ..... 10
የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት ..... 10
3.4 የሕግ አወጣጥ ሂደት ..... 11
የሕግ አወጣጥ ሂደት ግብና ዝርዝር ተግባራት ..... 11
3.5 ክትትል፣ ቁጥጥርና ድጋፍ ..... 12
የክትትል፣ ቁጥጥርና ድጋፍ ግብና ዝርዝር ተግባራት ..... 12
ዝርዝር ተግባራት ..... 12
3.6 የባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮች ግብ እና ዝርዝር ተግባራት ..... 15
ዝርዝር ተግባራት ..... 15
3.7 የቅሬታ ጉዳዮች ግብና ዝርዝር ተግባራት ..... 16
3.8 የመረጃ መሰብሰብና ማደራጀት ግብና ዝርዝር ተግባራት ..... 16
3.9 የዲሞክራሲ አስተሳሰብ ግብና ዝርዝር ተግባር ..... 17
ክፍል አራት ..... 18
4 የመስክ ምልከታ ..... 18
4.1 መደበኛ የመስክ ምልከታ ..... 18
4.2 የመስክ ምልከታ የሚካሄድባቸው ክልሎች ..... 18
4.3 በ2014 በጀት ዓመት በምንከታተላቸው ሁለት ሚ/ር መ/ቤቶች እና ተጠሪ ተቋማት የመስክ ምልከታ ይደረጋል ..... 18
4.4 የክዋኔ ኦዲትን በተመለከተ ..... 19
4.5 የቅንጅት ስራዎች ..... 19
ከፕላን፣በጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ጋር የሚሰሩ ስራዎች ..... 19
ከግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ጋር የሚሰሩ ስራዎች ..... 19
4.6 የአፈጻጸም አቅጣጫዎች፣ የክትትልና ድጋፍ ስርዓት ..... 19
የአፈጻጸም አቅጣጫዎች ..... 19
የክትትልና ድጋፍ ስርዓት ..... 20
4.7 የሚያጋጥሙ ስጋቶችና መፍትሄዎች ..... 20
ስጋቶች ..... 20
መፍትሄዎች ..... 20
5. ማጠቃለያ ..... 21
የድርጊት መርሀግብር ..... 23

# ክፍል አንድ

## 1. መግቢያ

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባወጣው የስነ-ምግባር ድንብ ቁጥር 6/2008 በተሻሻለው ንዑስ አንቀፅ 216 መሠረት በስራ ዘመኑ ከተቋቋሙት 11 ቋሚ ኮሚቴዎች ውስጥ አንዱ የሆነው የውሃ፣ መስኖ፣ ቆላማ አካባቢና አካባቢ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሲሆን ህግመንግስታዊ ሃላፊነቱን በአግባቡ ለመወጣት ከተሰጡት ተልዕኮዎች አንዱ አስፈፃሚ አካላት መከታተል፣ መቆጣጠርና መደገፍ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በዚሁ መሰረት የውሀ፣ መስኖ፣ ቆላማ አካባቢና አካባቢ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በስሩ እንዲከታተላቸዉና እንዲቆጣጠራቸዉ ብሎም እንዲደግፋቸዉ የተሰጡት አስፈፃሚ መ/ቤቶች የሚከተሉት ናቸዉ፡፡

እነርሱም፡- መስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር፣ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን፣ ውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴርና ተጠሪ ተቋማት፡- ታላቁ ህዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ፕሮጀክት ጽ/ቤት፣ የኢትዮጵያ ውሀ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት፣ ብሄራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት፣ ሲሆኑ የተሰጣቸውን ህዝባዊና መንግስታዊ ኃላፊነት ለመወጣት በዋና ሰብሳቢና ም/ሰብሳቢ በመደረጀት ሚኒስቴር መ/ቤትንና ተጠሪ መ/ቤቶችን በመከፋፈል፣ የክትትል፣ የቁጥጥርና ድጋፍ ተግባራት በተቋቋሙበት አዋጅና በወጡ ህጎችና አሰራሮች መሰረት መከናወናቸውን የተመደበውን የመንግስት በጀትና የህዝብ ሃብት ከኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰብ ተግባር በመታገል የተጀመራውን የመልካም አስተዳደር ስርዓት ግንባታ በማጠናከር የሕዝባችን ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ አቅደን መስራት ይጠበቅብናል፡፡

በሀገራችን ባለው ወቅታዊ የፀጥታ መደፍረስ ምክንያት እየተከሰተ ያለው ግጭት እየጨመረ የመጣው የኑሮ ውድነትና የዋጋ ግሽበት እንዲሁም የኮቪድ 19 ወረርሽኝ እያደረሰ ያለው ከፍተኛ ጉዳት በ2014 በጀት ዓመት የዕቅዱ መሳካት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡

የ2013 በጀት ዓመት በ10 ዓመቱ መሪ የልማት ዕቅድ ላይ ዕቅዶቹ ሙሉ በሙሉ ለመተግበር ተግዳሮቶች የገጠሙት ሲሆን የ2014 በጀት ዓመት ውስጥ ተመልሶ ታቅዶ እንዲፈፀም ትልቅ ርብርብ የሚደረግበት በመሆኑና የ2013 ዓ.ም በተፈጥሮ ሀብት መስኖና ኢነርጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴው የተከናወኑት ተግባራትና የተገኙ ልምዶችን ክትትል

፣ቁጥጥርና ድጋፍ ለመስጠት እንዲሁም ህግ በማውጣት የህዝብ ውክልናና የፓርላማ ዲፕሎማሲ ስራን ተልዕኮውን ውጤታማ በሆነ መንገድ አጠናክሮ ለመቀጠል የ2014 በጀት ዓመት እቅድ እንደሚከተለው ተዘጋጅቷል፡፡

## 1.1 የውሃ፣ መስኖ፣ ቆላማ አካባቢና አካባቢ ጥበቃ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

ውሃ፣ መስኖ ቆላማ አካባቢ እና አካባቢ ጥበቃ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በሚከተሉት ጉዳዮች ክትትልና ቁጥጥር ያከናውናል፡-

1/ ውሃና ኢነርጂን የሚመለከቱ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን እና ህጎችን መቀረፃቸውን፣ አፈጻጸሙ ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ መሆኑን፤

2/ የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደርን በተፋሰሶች ውስጥ ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር የሚረዱ የፖሊሲ ጥናቶችን፣ ቅኝቶችንና ምርምሮችን መደረጋቸውንና መፈፀማቸውን፤

3/ በተፋሰሶች ውስጥ የሚተገበሩ ከውሃ ጋር የተገናኙ ፕሮጀክቶችና እንቅስቃሴዎች ከተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር ሂደቶች ከውሃ ሀብት ስትራቴጂክ እቅድ እና ተግባራትን ለመምራትና ለመደገፍ የሚያስችል የተፋሰስ ሞዴል መዘርጋቱን፤

4/ የአገሪቱን የከርሰ ምድርና ገጸ ምድር የውሃ ሀብት በመጠንና በጥራት ጥቅም ላይ የሚውልበትን ሁኔታ መመቻቸቱን፤ በውሀ አጠቃቀም ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሃ ግብሮችን መቀረፃቸውንና ተግባራዊ መደረጉን፤

5/ ፍትሃዊ የውሃ አጠቃቀምን ለማስፈን የሚያግዝ ዘላቂ እና የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር ሥርዓት መፈጠሩን፤

6/ የውሃ ሃብት፣ የአካባቢ ጥበቃ ልማትና አጠቃቀምን አቅርቦት እድገትና ስርጭትን፤

7/ የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ሽፋን እንዲያድግ እገዛ መደረጉን ፣ የአማራጭ ኢነርጂ ምንጮችና ቴክኖሎጂዎች ልማት እንዲስፋፋ መደረጉን እና የመካከለኛና ከፍተኛ መስኖ ልማት ለማስፋፋት የሚያስችሉ የጥናት፣ የዲዛይን እና የግንባታ ሥራዎች በአግባቡ መከናወናቸውን፤

8/ የሜቲዎሮሎጂ አገልግሎት ሥራ በአግባቡ መከናወኑን፣ እና ለአገሪቱ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገት አስተዋፆ እያበረከተ መሆኑን፤

9/ የሀገሪቱ የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ለዘላቂ ልማት መርሆችን በተከተለ አግባብ መሆኑ፤

10/ የአካባቢ ደህንነትና ጥበቃ ዓላማዎችና ፖሊሲዎች በስራ ላይ መዋላቸውንና ውጤታማነታቸው መረጋገጡን፤

11/ የልማት ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች በአካባቢ ተፅኖ ግምገማ ስርዓት መሰረት ተግባራዊ መሆናቸው፤

12/ የመስኖ ልማት፣ የቆላማ፣ እና ለድርቅ ተጋላጭ የሆኑ አካባቢዎች እና የአርብቶ አደር ልማትን የሚመለከቱ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎች፣ ህጎች መዘጋጀታቸውን፣ አፈጻጸሙ ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን፤

13/ የመስኖ ልማት መስፋፋታቸውን፤

14/ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶችን ምርታማነት በሚያሳድጉ ወቅታዊ ቴክኖሎጂዎች መደገፋቸውንና ውሃ ቆጣቢ አሠራር መከተላቸውን፤

15/ በተቀናጀ የተፋሰስ ልማት በውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ጥናት የተለዩ የሀገሪቱን የከርሰ ምድር እና የገፀ ምድር የውሃ ሃብት ለመስኖ ልማት መዋላቸውን፤

16/ የመስኖ ልማት ሽፋን እንዲያድግ የሚያደርግ የአሠራር ሥርዓት መዘርጋቱን፤

17/ በመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች የአካባቢው ህብረተሰብ ተሳታፊና ተጠቃሚ መሆናቸውን፤

18/ በቆላ አካባቢዎች ያለውን የመስኖ ልማት አቅም የአካባቢውን የግብርና መሬት ለማልማት የሚያስችል የመስኖ ልማት ፕሮግራሞችን መቀረፁን፤

19/ አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ተጠቃሚ ለማድረግ የሚያስችሉ ተግባራት መከናወናቸውን፤

20/ የሚከታተላቸውና የሚቆጣጠራቸው ተቋማትን የሚመለከቱ ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ ስትራቴጂዎች እና እቅዶች በአግባቡ በሥራ ላይ መዋላቸውን፤ የሚከታተላቸውና የሚቆጣጠራቸው ተቋማት የተመደበላቸውን በጀት በአግባቡና በውጤታማነት በስራ ላይ ማዋላቸውን፡፡

## 1.2 የቋሚ ኮሚቴው ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ እሴቶች

### ሀ/ ራዕይ /Vision/

ሕገ-መንግስታዊ ኃላፊነቱን የሚወጣ የተለወጠ፣ ነፃ እና የሕዝቦችን ፍላጎት የሚወክል ውጤታማና ምላሽ ሰጭ ቋሚ ኮሚቴ መሆን፤

### ለ/ ተልዕኮ /Mission/

ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት መረጋገጥ የሚረዱ የህግ አወጣጥ ሥራዎችን መሥራት በአስፈጻሚ መሥሪያ ቤቶች ላይ የክትትል፣ ቁጥጥርና ድጋፍ ሥራዎችን ማከናወንና የህዝቡ የልካም አስተዳደርና የልማት ጥያቄ ፈጣን ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል የህዝብ ውክልና ተግባር በመፈጸም የህዝቡን ተጠቃሚነት ማረጋገጥና የተጠናከረ የፓርላማ ዲፕሎማሲ ሥራ በመሥራት የአገራችንን ገፅታ መገንባት ነዉ።

### ሐ/ ዕሴቶች / Values /

- ሕገ መንግስታዊነት
- ብዝሃነት፣ ወንድማማችነት እና እህትማማችነት
- ለብሔራዊ ጥቅም ቅድሚያ መስጠት
- መከባበርና የጋራ መግባባት
- ታማኝነትና ቁርጠኝነት
- ተደራሽነት፣ ምላሽ ሰጭነት እና ተጠያቂነት
- አካታችነት
- ለአረንጓዴ ልማት ተቆርቋሪነት

## 1.3 የእቅዱ ዋና ዓላማ

- በህዝባችን የተጣለብንን ኃላፊነት ለመወጣትና በሀገራችን የተጀመረውን ዕድገት ለማፋጠን ቋሚ ኮሚቴው የክትትልና ቁጥጥር ስራዎች በአሰራርና በተደራጀ መረጃ በህዝብ ተሳትፎ በዲሞክራሲ ተቋማት ሪፖርቶች በመታገዝ የሕግ የበላይነት እንዲከበር ተጠያቂነት እንዲሰፍንና የዜጎች መብቶች ጥቅሞች እንዲረጋገጡ ማድረግ ነው፡፡

### 1.4 የዕቅዱ ዝርዝር ዓላማዎች

- ለቋሚ ኮሚቴ ለዝርዝር ዕይታ እንዲጸድቁ የሚቀረቡ ረቂቅ ሕጎች፣ ፖሊሲዎችና እስትራቴጂዎች እንዲሁም የሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች ከህዝብ ተጠቃሚነት አንፃር በታቀደ መንገድ በህዝብ ተሳትፎ እንዲወጡ ማድረግ
- የቋሚ ኮሚቴውን የክትትልና ቁጥጥር ሥራዎች በአሰራር፣ በተደራጀ መረጃ፣ በህዝብ ተሳትፎ፣ በዲሞክራሲ ተቋማት ሪፖርቶች በመታገዝ የሕግ የበላይነት እንዲከበር፣ ተጠያቂነት እንዲሰፍንና የዜጎች መብቶችና ጥቅሞች እንዲረጋገጡ ማድረግ፣
- የሕዝብ ውክልና ሥራዎች ሲካሄዱ የሀገሪቷን የፀጥታ ሁኔታ፣ የኑሮ ውድነትና የዋጋ ግሽበት፣ የኮቪድ-19 ወረርሽኝን ትኩረት ባደረገ መልኩ እንዲሁም የፓርላማ ድፕሎማሲ ሥራዎችን በሕግ ማዕቀፍ እና በሙያዊ ድጋፍ በማጠናከር ውጤታማ ሥራ እንዲሰራ ማድረግ፣

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## 2. የዕቅዱ መነሻ ሁኔታዎች ግምገማ

### 2.1 የተፈጥሮ ሀብት መስኖና ኢነርጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የ2013 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም እንደ መነሻ

የ2013 በጀት ዓመት ዕቅድ በተቀመጠው ጊዜና ሰዓት እየተሰራ የቆየ የነበረ ሲሆን የcovid-19 ወረርሽኝን ከግምት ውስጥ በማስገባት እና የጤና ሚኒስቴርና መንግስት የሚያወጡትን የጥንቃቄ መውሰጃ መመሪያዎችን በመተግበር የቋሚ ኮሚቴው የክትትል፣ ቁጥጥር፣ የህግ አወጣጥና የህዝብ ውክልና ሥራዎችን በቋሚ ኮሚቴ አመራሮችና አባላት ተገምግሞ ጥንካሬና ድክመቶች ተለይተው የሶስት ወር፣ የስድስት ወርና የዘጠኝ ወር አፈፃፀም ቋሚ ኮሚቴው ጠንካራ ጐኖች ተጠናክረው የሚቀጥሉበትና እጥረቶች ታርመውና ተስተካክለው ቀጣዩን የዕትዕ 5ኛ ዓመት ግቦቻችንን ለማሳካት ወሳኝ ርብርብ የሚጠይቅ ጊዜና የ5 ዓመቱን የእድገትና ትራንስፎርሚሽን እቅድ ለማሳካት የሚያስችል ምቹ ሁኔታዎችን እንዲፈጥር ተደርጓል፡፡

### 2.2 አቅም ግንባታ ተግባራት አፈጻጸም

የተፈጥሮ ሀብት መስኖና ኢነርጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በ2013 በጀት ዓመት ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል አቅም ለመፍጠር በቋሚ ኮሚቴው በራሱ እንዲሁም በሌሎች

አስፈጻሚ አካላት መ/ቤቶች የተዘጋጁ በርካታ የአቅም ግንባታ ተግባራት የተከናወኑ ሲሆን ከነዚህም የአቅም ግንባታ መድረኮች፣ የቋሚ ኮሚቴው አመራርና አባላት ለተልዕኳቸው አጋዥ የሆኑ ግንዛቤዎችን አግኝተዋል፡፡ ተሳትፎ የተደረገባቸው የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ሲሆን ለአብነት፣ የብሄራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ የበጋ ወቅት የአየር ጠባይ አዝማሚያ ግምገማ፣ የውሃ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር የ2013 ዕቅድ ግምገማ፣ ውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት የግማሽ ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ፣ የመንግሥት የ10 ዓመት የልማት ዕቅድ፣ የረዥምና መካከለኛ ጊዜ የኢኮኖሚና ማሕበራዊ ዘርፍ ዕቅዶች፣ ፖሊሲዎች፣ አዳዲስ የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራሮች፣ እንዲሁም ማዕድንና ተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀም የመሳሰሉት  ይጠቀሳሉ፡፡

በመድረኮቹም አባላትና የቋሚ ኮሚቴው አመራሮች ሰፊ ግንዛቤ በመጨበጥ ሥራዎች ተጠናክረው እንዲሰሩ የበኩላቸውን አዎንታዊ አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡

### 2.3 የሕግ ማውጣት ተግባራት አፈጻጸም

የተፈጥሮ ሀብት መስኖና ኢነርጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የሚከታተላቸው ሴክተር መ/ቤቶች በ2013 በጀት ዓመት ወደ ፓርላማው በመላክ በዝርዝር በመመርመር የውሳኔ ሃሣብ ተዘጋጅቶ ይፀድቃል ተብለው ታቅደው የነበሩ የተለያዩ ፖሊሲዎችና ህጎች በወቅቱ ወደ ም/ቤቱ ባለመላካቸው በዕቅዱ መሠረት ተግባራዊ መሆን አልቻለም፡፡

ለአብነት፡-የውሃ አጠቃቀም ህግ በ2013 በጀት ዓመት ታቅዶ ያልተፈፀመ መሆኑ

### 2.4 የክትትልና ቁጥጥር ተግባራት አፈጻጸም

የተፈጥሮ ሀብት መስኖና ኢነርጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በ2013 በጀት ዓመት ያደርግ በነበረው የቁጥጥር፣ ክትትልና የድጋፍ ተግባር አብዛኞዎቹ መ/ቤቶች የቋሚ ኮሚቴውን ግብረ መልስ ተቀብለው ተግባራዊ ያደረጉ ቢሆንም በተደረገላቸው ድጋፍ የተለዩ ችግሮችን አውቀው ለውጥ ያላመጡ ተቋማት መኖራቸው እንዳለ ሆኖ በ2013 በጀት ዓመት በቋሚ ኮሚቴው አባላት በዋነኝነት አስፈፃሚ አካላትን የመቆጣጠር የመከታተልና የመደገፍ ስራ በስፋት ተሰርቷል፡፡

በሀገራችን የተከሰተው የጸጥታ ችግር፣ የኑሮ ውድነትና የዋጋ ግሽበት የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ስጋቶች በክትትልና ቁጥጥር ተግባራት በተለይ የመስክ ሥራዎች እና የውይይት መድረኮች በታቀደው መሰረት እንዳይፈጸሙ እንቅስቃሴዎችን የገደበ ቢሆኑም በተቻለ

መጠን በሥራ ላይ የሚያስከትሉትን አሉታዊ ጫና ለመቀነስና ለመፈጸም ከእነውስንነቱም ቢሆን በርካታ ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡

<u>ለአብነት፡-</u> በክልል የመስክ ምልከታም በኦሮሚያ፣ በሲዳማ፣ በጌዲዮ ዞን፣ በተደረገ የመስክ ምልከታ በተለይም በቋሚ ኮሚቴው ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ ይታያሉ ከተባሉ የንፁህ መጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን የመስኖ ልማት ስራ ፕሮጀክቶች ያለበት ደረጃ፣ እንዲሁም ከፕሮጀክት ጋር የሚያያዙ የአካባቢው ጥበቃ ስራዎች የሚሰሩበትን ቦታ በመስክ ምልከታው ታይቷል፡፡

## 2.5 የባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮች አፈጻጸም

የባለዘርፈ ብዙ ጉዳዮችን አፈጻጸም በተመለከተ በመስክ ምልከታዎችና የአፈጻጸም ሪፖርት ግምገማዎች ወቅት የስርዓተ-ጾታ ጉዳይ፤ የአካል ጉዳተኛና ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ተግባራት፣ የህፃናት ማቆያ እና የአከባቢ ጥበቃ ጉዳዮች የትኩረት ነጥቦች በመሆናቸው በዕቅድ ተካተው ስለመፈጸማቸው የመከታተል፣ ሰላምና ፀጥታን ለማስከበር ለተሰማራው የፀጥታ ሃይል ህይወት ለመታደግ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የደም ልገሳ የቋሚ ኮሚቴው አባላትና የቋሚ ኮሚቴው ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች እንዲሳተፉ የማድረግ፣ የዓለም የኤድስ ቀን፣ የፀረ ፆታ ጥቃት (ነጭ ሪባን) ቀን፣ ከፌዴራል ኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት፤ ከሴቶች ወጣቶችና ህጻናት ሚ/ር እና ከህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽ/ቤት ጋር በመተባበር የቋሚ ኮሚቴው አባላትና ሰራተኞች በተገኙበት ውይይቶችን በማካሄድ በጉዳዩ ላይ ግንዛቤ የመፍጠር ተግባራት ተከናውነዋል፡፡

## 2.6 የተፈጥሮ ሀብት መስኖና ኢነርጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የ2013 በጀት ዓመት አፈፃፀም ጥንካሬዎችና ድክመቶች

### ሀ/ በቋሚ ኮሚቴው የነበሩ ጥንካሬዎች

- የቋሚ ኮሚቴው አባላት በተለያዩ ምክንያቶች ሲጓደሉ ስራዉን በተገኙት አባላት ሸፍኖ የመስራት ተግባራት መከናወናቸው፤
- COVID-19ን ለመከላከል የሚያስችሉ የመከላከያ ማቴሪያሎች በቋሚ ኮሚቴው ልዩ ልዩ ስብሰባዎች በሚካሄዱባቸው አዳራሾች በማመቻቸት ተሰብሳቢዎች እንዲጠቀሙ መደረጉ፤

- የቋሚ ኮሚቴው አባላት በተወሰኑ የአገራችን አከባቢዎች የሚከሰቱ የፀጥታ ችግሮችን ተቋቁመውና የኮረና ቫይረስ ወረርሽኝ ስጋትን ለመከላከል የወጣውን መመሪያ መሰረት ባደረገ መልኩ ዕቅዶች ሳይንጠባጠቡ እንዲፈጸሙ ጥረት መደረጉ፣
- የአስፈጻሚ መ/ቤቶችን ሪፖርት ግምገማ እና የመስክ ግኝቶችን በማደራጀት ለሚመለከታቸው አስፈፃሚ አካላት በማቅረብ ምላሽ እና ማብራሪያ እንዲሰጡበት መደረጉ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

### ለ/ በቋሚ ኮሚቴው የነበሩ ድክመቶች

- የቋሚ ኮሚቴው አባላት በተለያዩ ምክንያቶች ከስራ መጓደልና ተሟልቶ አለመገኘት፣
- በክልሎች የመስክ ስምሪት እና ከተማ ውስጥ የተቋማት ስብሰባ ሲጠራ አልፎ አልፎ ችግሮች ማጋጠማቸውና ከተሽከርካሪዎቹ ማርጀት ጋር በተያያዘ በመስክ ስራ ስምሪት ላይ ችግሮች የተስተዋሉ መሆኑ፤

## 2.7 ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች፤

### ሀ/ ያጋጠሙ ችግሮች

- ተጠሪ ተቋማት በቋሚ ኮሚቴው የሚሰጡትን ግብረ መልሶች ተቀብለው መተግበርና የወሰዱቸውን ማስተካከያዎች ማሳወቅ ላይ ውስንነቶች መኖራቸው፣
- ሃገራዊ የፀጥታ ሁኔታ በመደበኛ ሥራዎች ላይ ተጽዕኖ መፍጠሩ፡
- አቤቱታ የሚቀርብበትና መፍትሄ የሚሰጥበት አሰራር ስርዓት ያልተዘረጋለት መሆኑ በቋሚ ኮሚቴው ስራ ላይ ጫና መፍጠሩ፣

### ለ/ የተወሰዱ መፍትሄዎች

- ተቋማት የሥራ እቅዳቸውን፣ሪፖርትና የግብረ-መልስ አፈጻጸም በወቅቱ እንዲልኩ በጋራ ውይይት መግባባት ላይ ለመድረስ ጥረት ተደርጓል ፡፡
- የመስክ ምልከታ ፕሮግራሞችን የቦታ ማሻሻያ እና የትኩረት አቅጣጫ ለውጥ በማድረግ ወቅታዊውን ሁኔታ ባገናዘበ መንገድ ክትትል ተደርጓል፣
- ከአቤቱታ እና ቅሬታ አፈታት ጋር በተያያዘ ችግሩን ለመፍታት ጥናት እየተከናወነ ይገኛል፡፡

# ክፍል ሶስት

## 3. የውሃ፣ መስኖ፣ ቆላማ አካባቢና አካባቢ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የ2014 በጀት ዓመት መሪ ዕቅድ

### 3.1 የቋሚ ኮሚቴው ቁልፍ ተግባር

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት ለቋሚ ኮሚቴው በተሰጠው ስልጣንና ተግባር መሠረት በሚደረገው ቁጥጥር፣ ክትትልና ድጋፍ ህዝብን ተጠቃሚ ያላደረጉ ተቋማት ህብረተሰቡን ተጠቃሚ እንዲያደርጉ ማድረግና ይህንን ያልፈፀሙ መ/ቤቶች ላይ ተጠያቂነትን ማስፈን፣

### 3.2 የዝግጅት ምዕራፍ

<u>**ግብ፡-**</u> የቋሚ ኮሚቴውን የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድና ቼክሊስት አዘጋጅቶ ማፅደቅና ከአስፈፃሚ መ/ቤት አመራሮች ጋር የትውውቅ ፕሮግራም ማዘጋጀት

**የሚጠበቅ ውጤት፡-** ጥራቱን የጠበቀና ተፈፃሚነት ያለው ዕቅድና ቼክሊስት እንዲሁም ለስራው ኃላፊነት በመውሰድ ተጠያቂነትን ማረጋገጥ

**የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት**

- ቋሚ ኮሚቴው ለ2014 በጀት ዓመት የራሱን ዕቅድ የሚያዘጋጅ ሲሆን ለክትትልና ቁጥጥር ተግባራት በተለይ ለአስፈጻሚ መ/ቤቶች እቅድ አፈጻጸም ግምገማ ይረዳ ዘንድ የሥራ ባህሪውን ያገናዘበ ቼክ-ሊስት የሚዘጋጅ ይሆናል፣
- ለቋሚ ኮሚቴው አባላት ሰብሳቢና ለምክትል ሰብሳቢ እንዲሁም ለድጋፍ ሰጪ ባለሙያች የትውውቅ ፕሮግራም ይዘጋጃል፡፡
- ከውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴርና ከመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር አመራርና ሰራተኞች ጋር በቋሚ ኮሚቴ ደረጃ የተቋቋመው የውሃ፣ መስኖ፣ ቆላማ አካባቢ እና አካባቢ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት የትውውቅ መርሀ ግብር ይካሄዳል፡፡
- ለቋሚ ኮሚቴው የስራ አካሄድ ይረዳ ዘንድ ለአባላት የሚያስፈልጉ ልዩ ልዩ የስራ መገልገያዎች እንሟሉ ማድረግ
- ለቋሚ ኮሚቴው የስራ ክፍፍል ማድረግ ወይም በንዑስ ኮሚቴ ደረጃ ስራዎችን መስኬድ

## 3.3 የተግባር ምዕራፍ

### አቅም ግንባታ

ግብ 1 የቋሚ ኮሚቴውን አባላት አቅም መገንባት

የሚጠበቅ ውጤት፡-የጎለበተና የቋሚ ኮሚቴውን የህግ ማውጣት፣ ክትትልና ቁጥጥር፣ የውክልና የፓርላማ ዲፕሎማሲ ስራዎችን መፈፀም ያስቻለ አቅም

### የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት

- የቋሚ ኮሚቴውን ውጤት መሰረት ያደረጉ የአስፈጻሚ አካላት የዕቅድ እና የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማዎችና ውይይቶችን እንዲሁም በረቂቅ ሕጎች ምርመራ ሂደት የሚደረጉ ክርክሮችን እንደ አንድ የአቅም ግንባታ መሳሪያ ተደርጎ እንዲወሰድ የማመቻቸት ሥራ የሚሰራ ይሆናል፤
- የቋሚ ኮሚቴው አባላት በሚከታተላቸው አስፈፃሚ መ/ቤቶች በኩል የሚካሄዱ ስልጠናዎች በተለይም በንፁህ መጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ለህብረተሰቡ ያለው ተደራሽነትና ያሉበት ተግዳሮቶች፣ በመስኖ ልማት ዘርፍ የመስኖ ውሃ አጠቃቀም ሂደት ተግዳሮቶችና መልካም አጋጣሚዎች፣ የአካባቢ ጥበቃና የአየር ንብረት ለውጥ መልካም አጋጣሚዎችና ተግዳሮቶች፣ የብሄራዊ ሚቲዎሮሎጂ ጣቢያ ተደራሽነትን በተመለከተ ስልጠና እንዲያገኙ ይደረጋል
- ልዩ ልዩ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ላይ ለምሳሌ፡- በአካባቢ ልማትና ጥበቃ ፖሊሲና ስትራቴጂ፣ የአየር ንብረት ለውጥ ፖሊሲና ስትራቴጂ፣ የንፁህ መጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ፖሊሲና ስትራቴጂ፣ የመስኖ ልማት ዘርፍ ፖሊሲና ስትራቴጂ፣ የብሄራዊ ሚቲዎሮሎጂ ፖሊሲና ስትራቴጂ ላይ የአባላትን አቅም ሊያጎለብቱ ስለሚችሉ ስልጠናው ይሰጣል፡፡
- የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደርንና አጠቃቀምን፣ የመስኖ ልማት ስራዎች፣ የተፋሰሶችን ልማትን በተመለከተ ከባለድርሻ አካላት ጋር የምክክር መድረክ ይዘጋጃል
- የአካባቢ ጥበቃ እና የአካባቢ ህግ ተከባሪነት ማጎልበት ዙሪያ ከባለድርሻ አካላት ጋር የምክክር መድረክ ይዘጋጃል
- ከምንከታተላቸው መ/ቤቶች ውስጥ ለቋሚ ኮሚቴው ለክትትልና ቁጥጥር ይበልጥ አቅም ሊፈጥሩለት የሚችሉ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች በቋሚ ኮሚቴው አዳራሽ በኮሚቴው

አመራሮችና አባላት እንዲሁም የተጠሪ ተቋማት ኃላፊዎችና ባለሙያዎችን በመታገዝ ስልጠና እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

- አባላት የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስልጠና፣ የመረጃ አያያዝ ዘዴ፣ የሪፖርት አዘገጃጀትና አተገባበር፣ መሰረታዊ የተግባቦት ክህሎት በሚሉ ርዕሶች ዙሪያ ስልጠና እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

## 3.4 የሕግ አወጣጥ ሂደት

### የሕግ አወጣጥ ሂደት ግብና ዝርዝር ተግባራት

<u>ግብ 2</u> ለቋሚ ኮሚቴው የተመሩ ረቂቅ ሕጎች የህብረተሰቡን ተሳትፎና ተፈጻሚነትን እንዲሁም አግባብነትና ጥራትን ባረጋገጠ መልኩ እንዲፀድቁ ማድረግ፣

**የሚጠበቅ ውጤት፡-**

1. በጥልቀት ተመርምረው የጸደቁ ተፈጻሚና ህዝብን ተጠቃሚ ያደረጉ ጥራት ያላቸው ህጎች፤
2. ከጸደቁት ሕጎች ጋር ተጣጥመው የወጡ ደንቦችና መመሪያዎች፤

### ዝርዝር ተግባራት

- የፀደቁ አዋጆች በነጋሪት ጋዜጣ ወደታች በማውረድ ግንዛቤ ለህብረተሰቡ እየተፈጠረ መሆኑን አቅጣጫ መስጠትና መከታተል፣
- ከም/ቤቱ ለቋሚ ኮሚቴው ለዝርዝር እይታ የተመሩ ረቂቅ አዋጆችና ደንቦች በጥልቀት እንዲመረመሩ፣ ለምርመራ በሚቆዩበት ወቅትም የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት አስተያየታቸውን እንዲሰጡ እንዲሁም ልዩ ልዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በሕዝብ ይፋዊ ውይይት መድረክ ተገኝተው እንዲሳተፉ ማድረግ
- ከም/ቤት ለቋሚ ኮሚቴው ለሚመሩ ረቂቅ ሕጎች ምርመራ የሚያግዝ የረቂቅ ሕጎች መገምገሚያ ስታንዳርድ የሚዘጋጅና በውይይት ዳብሮ የሚተገበር ይሆናል፤
- በበጀት ዓመቱ ሕግ ሆነው ይወጣሉ ተብለው የሚገመቱ ዝርዝር ረቂቅ አዋጆችና ደንቦችን ከሚመለከተው ክፍል በወቅቱ በመቀበል ሕግ ሆነው መውጣታችውን፣ እንዲሁም ሕጉን ተከትለው መውጣት የሚገባቸው ደንቦችና መመሪያዎች ወጥተው ስራ ላይ መዋላቸውን የመከታተል ሥራዎች ይሰራሉ፤

- በህግ አወጣጥ ዙሪያ ለቋሚ ኮሚቴው የሚመሩ ረቂቅ አዋጆችንና የትብብር ስምምነቶችን መመርመር፤ ይህም ለህግ አወጣጥ ሂደቶቹ ምቹ መድረኮችን በመፍጠር የሚከናወን ይሆናል፡፡
- ለቋሚ ኮሚቴው በሚመሩ ረቂቅ አዋጆችና የትብብር ስምምነቶች ላይ በቋሚ ኮሚቴው አባላት ውይይት ይደረግበታል፡፡
- አዋጅ ደንብና መመሪያን በተመለከተ፤ ቋሚ ኮሚቴው ከሚከታተላቸው አስፈፃሚ መ/ቤቶች መካከል አዋጅ፣ደንብና መመሪያ የሚያስፈልጋቸውን መ/ቤቶች በመለየት እና መረጃ በመያዝ አዋጅ፣ ደንብ እንዲሁም መመሪያዎች ያልወጣላቸው እንዲወጣላቸው ክትትል ይደረጋል፤

## 3.5 ክትትል፣ ቁጥጥርና ድጋፍ

### የክትትል፣ ቁጥጥርና ድጋፍ ግብና ዝርዝር ተግባራት

<u>ግብ 3</u> ቋሚ ኮሚቴው የሚከታተላቸው አስፈጻሚ መ/ቤቶች ዕውቀትን እና መረጃን መሠረት ያደረጉ የተቀናጁና ውጤታማ የሆኑ የክትትል፣ ቁጥጥርና የድጋፍ ተግባራትን ማከናወን፣

**የሚጠበቅ ውጤት፡-**

1. ያደገ የህዝብ ተጠቃሚነት እና ተጠያቂነት፣

**ዝርዝር ተግባራት**

- የአስፈጻሚ አካላት ዕቅዶች የመንግሥትን የበጀት ዓመት አገራዊ መሪ ዕቅድና የትኩረት አቅጣጫዎችን ታሳቢ አድርገው የተዘጋጁና የተፈጸሙ መሆናቸውን በማረጋገጥ ግብረ-መልስ የሚሰጥና ለግብረ-መልስ አፈጻጸሙም ክትትል የሚደረግ ይሆናል፡፡
- ሕብረተሰቡን ተሳታፊና ተጠቃሚ ያደረጉ የአስፈጻሚ አካላት የዕቅድ አፈፃፀሞች በተቀናጀና በተደራጀ አግባብ በከተማና ከከተማ ውጭ በመስክ ምልከታ የሚረጋገጡበት አሰራር ተጠናክሮ የሚፈጸም ይሆናል፤
- ከክትትልና ቁጥጥር ስልቶች አንዱ በሆነው በመስክ ምልከታ ግኝቶች በተለይ በዋና የፕሮጀክቶች አፈጻጸም ላይ ትኩረት ያደረገ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ግብረ-

መልስ የመስጠት፣ በሂደቱም መታረም ያለባቸው እንዲታረሙና መጠናከር ያለባቸው እንዲጎለብቱ የማድረግ ሥራዎች በትኩረት ይሰራሉ፣

- የአስፈጻሚ አካላት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርቶች፣ የመስክ ምልከታ ሥራዎች፣ የቃል መልስ የሚሰጥባቸው ፕሮግራሞች ለክትትልና ቁጥጥር እንደግብዓት ተወስደው በበጀት ዓመቱ በትኩረት የሚከናወኑ ይሆናል፡፡
- በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የኦዲት ግኝት ሪፖርት መሰረት በኦዲት ተደራጊ የመንግስት መ/ቤቶችና ድርጅቶች የተወሰዱ የማስተካከያ እርምጃዎችና የተገኙ ውጤቶች ስለመኖራቸው እና ስለመሻሻሉ የሚያረጋግጡ የክትትልና የቁጥጥር ሥራዎች ተጠናክረው የሚከናወኑ ይሆናል፡፡
- በቃል መልስ የሚሰጥበትን የጥያቄ ጊዜ በተመለከተ ከቋሚ ኮሚቴ አባላት፣ ከተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች የሚነሱ፣ ከቋሚ ኮሚቴው ስልጣንና ተግባር ጋር ተያያዥነት ያላቸው ወቅታዊና አንገብጋቢ ጥያቄዎች፣ ከመስክ ምልከታ የተገኙ መረጃዎች፣ የሃገር ደህንነትና የሕዝብ ሰላም ጉዳዮች፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ጥያቄዎች በሕጉ መሰረት በሚመለከተው ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ሃላፊ ተገቢውን ምላሽ እንዲያገኙ የሚያስችል የቃል መልስ የሚሰጥበት ስርዓት በተጠናከረ ሁኔታ የሚፈጸም ይሆናል፡፡
- ለቋሚ ኮሚቴው ቀጥታ ተጠሪ የሆኑ ተቋማት በአገራችን የተከሰተውን የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ በሽታን ለመግታት በእቅዳቸው አካተው በጥብቅ ዲስፕሊን ተግባራዊ እያደረጉ ስለመሆናቸው እንዲሁም ሴክተር ዘለል ተግባራትን በተመለከተም በዕቅዳቸው መሰረት ስለመፈጸማቸው በክትትልና ግምገማ ስርዓት ውጤታማነቱን የማረጋገጥ ሥራ በልዩ ትኩረት የሚሰራ ይሆናል፡፡
- አስፈጻሚ አካላት እና ለቋሚ ኮሚቴው ቀጥታ ተጠሪ የሆኑ ተቋማት ከክትትልና ቁጥጥር ሥራዎች አንጻር በም/ቤቱ የወጡ አዋጆች አስፈላጊ የሆኑ ደንቦችና መመሪያዎች ወጥቶላቸው ሥራ ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ እና ደንብና መመሪያ ላልወጣላቸው አዋጆች በሕጉ መሰረት በሦስት ወራት ውስጥ ደንብና መመሪያ እንዲወጣላቸው የሚያደርጉ የክትትልና ቁጥጥር ተግባራት ተጠናክረው የሚፈጸሙ ይሆናል፡፡
- የምንከታተላቸው አስፈፃሚ መ/ቤቶችን በአግባቡ ለመከታተል የመከታተያ ቅፅ/ቼክ ሊስት/ማዘጋጀት፣ የተዘጋጀውን ለአስፈፃሚዎቹ መላክ፣

- በአስፈፃሚ መ/ቤቶች ክትትልና ቁጥጥር ስራችን የመንግስት የ10 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ በአገር ደረጃ የተጀመረውን የሪፎርም ሂደት ንቅናቄው በቀጣይነት ውጤታማ እንዲሆን የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመፍታት ራሱን የቻለ ዕቅድ አቅደው እንዲተገብሩና የሕብረተሰቡን እርካታ በማምጣት ከኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰብና ተግባር በፀዳ መልኩ መተግባራቸውን መከታተል፣
- የቋሚ ኮሚቴው አባላትን አቅም የሚያጐለብቱና ለዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዳችን መሳካት ገንቢ ሚና ለመጫወት ቋሚ ኮሚቴው በራሱ ደረጃ በም/ቤቱ እና በሌሎች አካላት በሚዘጋጁ በተመረጡና ለስራችን ጠቀሜታ ያላቸው የተለያዩ ሥልጠናዎች ላይ በንቃት መሳተፍና ከሥልጠናው የተገኘዉን ዕዉቀትና ተሞክሮ ለሌሎች በማካፈል የጋራ አቅምን ማጠናከር፣
- በቋሚ ኮሚቴውና በአስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶች ዕቅድ ላይ በተመረጡት አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶች ጋር በአካል በመወያየት የጋራ ማድረግና በክትትል ቁጥጥር አግባብ ላይ ከስምምነት መድረስ፣
- በሚደረገው የክትትል ቁጥጥር ድጋፍ ስራችን ውስጥ በግልፅ በሚታዩና በመረጃ ላይ በተመሠረተ ለዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዳችን መሳካት እንቅፋት በሚሆኑ ብልሹ አሰራሮች የሥነምግባር ጉድለቶችና የሃብት ብክነቶች እንዲስተካከሉ ማድረግና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ክዋኔ ኦዲት ማስደረግ፣ በክዋኔ ኦዲቱ ግኝት መሠረት አስተያየት የተሰጠባቸው አስፈፃሚ መ/ቤቶች ማስተካከያ እንዲያደርጉ ማሳሰብ እና አፈፃፀማቸውን መከታተል።
- በበጀት ዘመኑ ሪፖርት የሚያቀርቡትን መለየት፣ የስራ ሪፖርቱን በቀጥታ ቋሚ ኮሚቴው በሚያወጣው ጊዜ ሰሌዳ በቂ ዝግጅት በማድረግ እንዲያቀርቡ መከታተል፣
- የተጠሪ ተቋማት ስትራቴጂክ እቅዳቸውንና የዓመቱን ዕቅድ በማነፃፀር ለዚህም ግብረ መልስ በመላክና በግብረ መልሱ መሠረት ዕቅዱ መስተካከሉን ይከታተላል፡፡
- አስፈፃሚ መ/ቤቶችን ለመከታተል ቋሚ ኮሚቴው የክትትልና ቁጥጥር ቼክ ሊስት አዘጋጅቶ በቼክሊስቱ መሰረት ስራዎች ይከናወናሉ፡፡
- የመስክ ምልከታ በማካሄድና ምልከታውን በዝርዝር በተዘጋጀ ቼክ ሊስት በአካል ሥራው ቦታ ድረስ ሄዶ በመከታተልና ሪፖርታቸውን መገምገም፡፡
- አስፈፃሚው በአካል በም/ቤቱ ወይም ለቋሚ ኮሚቴው ዓመታዊ ዕቅድ አፈፃፀማቸውን የሚያቀርቡ ይሆናል፡፡

- በህዝብ ቅሬታዎችና ጥያቄዎች በሚቀርቡበት ጊዜ ችግሩን ለመፍታት ቋሚ ኮሚቴው አስፈፃሚውን በመጥራት መልስ እንዲሰጡ ማድረግ፡፡
- የቋሚ ኮሚቴ አባላት ከም/ቤቱ ውጪ የሚያገኙትን አጫጭር ስልጠና በተመለከተ ለቋሚ ኮሚቴ አባላት አጭር ገለፃ እንዲያደርጉ በማድረግ ለቀሪ አባላት ያገኟቸውን ልምዶች እንዲያካፍሉ ይደረጋል፡፡

## 3.6 የባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮች ግብ እና ዝርዝር ተግባራት

**ግብ፡4** ቋሚ ኮሚቴው በሚከታተላቸው አስፈጻሚ አካላት ዕቅዶችና አፈጻጸም ሪፖርቶች የባለዘርፈብዙ ጉዳዮች የተካተቱና የተፈጸሙ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤

**የሚጠበቅ ውጤት፤** ቋሚ ኮሚቴው የሚከታተላቸው ተቋማት ዕቅዶችና አፈጻጸም ሪፖርቶች ውስጥ ተካተው ተጠቃሚነትን ያረጋገጡ የባለዘርፈ-ብዙ ጉዳዮች፤

### ዝርዝር ተግባራት

- አስፈፃሚ መ/ቤቶችና ተጠሪ ተቋማት የሴክተር ዘለል (Cross cutting issues) ተግባራትን በዕቅዶቻቸው በማካታት ከመደበኛ ተግባሮቻቸው እኩል ስለመተግበራቸው ክትትልና ቁጥጥርና በማድረግ ሕ/ሰቡ ተጠቃሚ የሚሆኑበት ሁኔታ እንዲጎለብት በትኩረት የሚሰራ ይሆናል፡፡
- ቋሚ ኮሚቴው በአስፈጻሚ አካላትና ተጠሪ ተቋማት ከዘርፈ ብዙ ተግባራት አፈፃፀም አኳያ ሊሰሩ የሚገባቸውን ስትራቴጅክ ጉዳዮች በጥናት የመለየት፣ አደረጃጀቶቹን የመፍጠርና የማጠናከር፣ በተሻለ የአመራር ትኩረት እንድፈፀም የማድረግ እና በእውቀት ላይ የተመሰረተ ድጋፍና ክትትል ማድረግ የሚያስችል አቅጣጫ በመከተል እንዲከናወኑ ያደርጋል፡፡
- ለቋሚ ኮሚቴው ተጠሪ የሆኑ አስፈጻሚ ተቋማት የህፃናትን መብት ለማክበር እና የሴት ሠራተኞችን ተሳታፊነት፣ የአካል ጉዳተኞች ተጠቃሚነት፣ የኤች አይቪ ኤድስ ስርጭትን ለመግታት እየተሰሩ ያሉ ስራዎች እንዲሁም የኮቪድ-19ን ታሳቢ ያደረገ የህፃናት ማቆያ ቦታዎች መዘጋጀታቸውን የመከታተልና የማረጋገጥ ሥራዎች ይሰራሉ፣

- ቋሚ ኮሚቴው በሚከታተላቸው አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶች የሀገሪቱ የፀጥታ ሁኔታን በተመለከተና ኮሮና ወረርሽኝ ለመከላከልና ለመቆጣጠር የታቀዱና የተሰሩ ሥራዎችን አፈጻጸም የመከታተልና የመቆጣጠር ሥራዎች በትኩረት ይሰራሉ፣

## 3.7 የቅሬታ ጉዳዮች ግብና ዝርዝር ተግባራት

ግብ፡- 5 ቅሬታና ጥቆማን መርምሮ ምላሽ መስጠት

የሚጠበቅ ውጤት፡- የህብረተሰቡን ችግር መፍታት

**ዝርዝር ተግባራት**

- ከክልልና ቋሚ ኮሚቴው ከሚከታተላቸው መ/ቤቶች የሚመጡ ጥቆማና ቅሬታዎችን ተቀብሎ ምላሽ መስጠት
- በስልክ፣ በፋክስ፣ በደብዳቤና በአካል የሚመጡ ቅሬታዎችና ጥቆማዎች ተቀብሎ በቋሚ ኮሚቴው አባላት በቂ ውይይት ተደርጎ እንዲፈቱ ማድረግ
- ም/ቤቱ ለቋሚ ኮሚቴው የሚመራውን የህዝብ ቅሬታና ጥቆማ ተቀብሎ በጥልቀት መከታተል
- ቋሚ ኮሚቴው ከመረጣቸው ህዝብ ዘንድ በመሄድ የምንከታተላቸውን የፌዴራል አስፈፃሚ መ/ቤቶችን በሚመለከት የሚያመጡዋቸውን ጥያቄዎች በማሰባሰብ እንደ ሁኔታው ከአስፈፃሚ መ/ቤቶች ጋር ውይይት በማድረግ ተፈፃሚነቱን መከታተልና መልስ እንዲያገኙ ማድረግ፤

## 3.8 የመረጃ መሰብሰብና ማደራጀት ግብና ዝርዝር ተግባራት

ግብ 6፡- መረጃ መሰብሰብና ማደራጀት

የሚጠበቅ ውጤት፡- የተደራጀ ሲፈለግ በቀላሉ ሊገኝ የሚችል ወቅታዊና ተዓማኒነት ያለው መረጃ ማግኘት

ዝርዝር ተግባራት

- ከአስፈፃሚ መ/ቤቶች በሃርድ ኮፒና ሶፍት ኮፒ የሚላኩ ዕቅዶች፣ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት፣ ከተለያዩ አካባቢዎች በስልክ፣ በፋክስ፣ በደብዳቤ፣ በአካል እንዲሁም ከም/ቤቱ ለቋሚ ኮሚቴው የሚመሩ ቅሬታዎችና ጥቆማዎች ተቀብሎ መረጃ መያዝ፣

- ቋሚ ኮሚቴው የሚከታተላቸውን አስፈፃሚ መ/ቤቶች የተቋቋሙበትን አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎችን ማደራጀት
- በንፁህ መጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን፣ በመስኖ ልማት ዘርፍ፣ አካባቢ ጥበቃን በተመለከተ የወጡ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን አደራጅቶ መያዝ
- በቋሚ ኮሚቴው ለአስፈፃሚ መ/ቤቶች በፅሁፍ የሚሰጡ ግብረ መልሶችን እንዲሁም ተቋማቱ የሚልኩትን የግብረ መልስ ግብረ መልስ አደራጅቶ መያዝ
- በቋሚ ኮሚቴ ደረጃ ለሚካሄዱ ስብሰባዎች ቃለ-ጉባኤ አደራጅቶ መያዝና መረጃዎቹ ሲፈለጉ በቀላሉ ማቅረብ
- የውሃ ሀብት መረጃና ኢንፎርሜሽን የማደራጀት ተግባር በስፋት ይከናወናል
- ከብሄራዊ ሚቲዎሮሎጂ የሚገኙ አገልግሎቶች ዘመናዊነትና የቴክኖሎጂ መሠረተ ልማቶችን በማስፋፋት ከዘርፉ የሚገኙትን መረጃዎች የመጠቀም አቅም ማሳደግ

## 3.9 የዲሞክራሲ አስተሳሰብ ግብና ዝርዝር ተግባር

ግብ 7፡- የዲሞክራሲ አስተሳሰብ ተግባርና ልምምድን በማስፈን የሴቶች፣ አካል ጉዳተኞችና ወጣቶችን ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ

የሚጠበቅ ውጤት፡- በህብረ ብሄራዊ አንድነት የሀገሪቱን የብልፅግና ጉዞ ማስቀጠል

ዝርዝር ተግባራት

- ያሉንን ልዩነቶች አስወግደን ወደ አንድነት በመምጣት ብዝሀነትን ባማከለ መልኩ ሀሳባችንን ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ወደ ግብ በማድረስ የተጀመረውን የብልፅግናና የለውጥ ጉዞ ማስቀጠል
- የምንከታተላቸው አስፈፃሚ መ/ቤቶች ዲሞክራሲን መሠረት ያደረጉ የሴቶች፣ አካል ጉዳተኞችና ወጣቶች ተጠቃሚነትን ያረጋገጠ ዕቅድ ማቀዳቸውን መከታተል
- በምንከታተላቸው አስፈፃሚ መ/ቤቶች ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞችና ወጣቶች አቅማቸውን ሊያጎለብት የሚችል ስልጠና እንዲያገኙ መስራት
- ቋሚ ኮሚቴው የሚሰጠው አገልግሎት በዲሞክራሲያዊ መንገድ ህብረተሰቡን በተለይም ሴቶችና አካል ጉዳተኞችን ተጠቃሚ ያደረጉና ተደራሽነት ያላቸው መሆናቸውን የማረጋገጥ ስራ በስፋት ይሰራል

# ክፍል አራት

## 4 የመስክ ምልከታ

### 4.1 መደበኛ የመስክ ምልከታ

የመደበኛ መስክ ምልከታ በፌዴራል መንግስት በጀት የሚከናወኑ እና በኮሚቴው ድጋፍ እና ክትትል የሚደረግባቸው ፕሮጀክትና ስራዎች በተቀመጠላቸው በጀት፣ጥራትና ጊዜ እየተከናወኑ መሆኑን በመገምገም የህብረተሰቡ ተጠቃሚነትና ባለቤትነት፣ የፕሮጀክቱ ደህንነትና ቀጣይነት፤እንዲሁም በአካባቢ ላይ ጉዳት እንዳይደርስ እየተሰራ ያለውን ስራ በመገምገም አስፈላጊውን የክትትል፣ የቁጥጥርና የድጋፍ ስራ ለመስራት ኮሚቴው የሚጠበቅበትን ኃላፊነት እንዲወጣ ማስቻል ነው፡፡ በ2014 በጀት ዓመት የመደበኛ መስክ ምልከታ የሚካሄድባቸው የሀገሪቱ ክፍሎች በተለይም የፕሮጀክቶች አፈጻጸም በሪፖርት ከተገለፀው ጋር መጣጣሙን ለማረጋገጥ፣ ፕሮጀክቶች በተቀመጠላቸው በጀት ጊዜ ጥራት መከናወናቸውን ለመገምገም፣ ፕሮጀክቶች የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት (EIA) መሠረት እየተሰራ መሆኑን ማረጋገጥ፣ ፕሮጀክቶቹ ለህብረተሰቡ የሚያስገኘው ጠቀሜታና የአካባቢው ህዝብ ባለቤት እንዲሆን የተሰራው ስራ ለመገምገምና ድጋፍ ለማድረግ አስፈጻሚ መ/ቤቶች እና የአካባቢው መስተዳደር ለፕሮጀክቶች የሚያደርጉት ክትትል ቁጥጥርና ድጋፍ በመገምገም እና በማረጋገጥ ድጋፍ መስጠት ይሆናል፡፡ በ2014 የመስክ ምልከታ የሚካሄድባቸው ክልሎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 4.2 የመስክ ምልከታ የሚካሄድባቸው ክልሎች

- በኦሮሚያ እና ደቡብ ክልሎች
- በአማራ እና ትግራይ ክልሎች /ያለው የፀጥታ ሁኔታ ታሳቢ ተደርጎ/
- በሶማሌ እና አፋር ክልሎች
- በድሬዳዋ እና ሀረሪ ክልሎች
- በቤኒሻንጉል ብሄራዊ ክልል

### 4.3 በ2014 በጀት ዓመት በምንከታተላቸው ሁለት ሚ/ር መ/ቤቶች እና ተጠሪ ተቋማት የመስክ ምልከታ ይደረጋል

- በውሀ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር እና ተጠሪ ተቋማት፡-
  - በውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት

- በብሄራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት
- በታላቁ ህዳሴ ግድብ ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽ/ቤት

➢ በመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር

➢ በአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ከኃላፊዎች ጋር እና ከሠራተኞች ጋር መወያየት

## 4.4 የክዋኔ ኦዲትን በተመለከተ

➢ በዋና ኦዲተር በ2013 ዓ.ም በም/ቤቱ የቀረቡ ግኝቶችን ቋሚ ኮሚቴአችን የሚከታተላቸውን ሴክተሮች ላይ የተቀመጡ ጉድለቶችና በ2014 በዋና ኦዲተር በተመሳሳይ ለምንከታተላቸው ሴክተሮች የሚመለከት ግኝት ላይ የዋና ኦዲተር ሀሳብን ተከትሎ ተግባራዊ እንዲያደርጉ ጥብቅ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ችግራቸውን እንዲቀርፉ ማስቻል፣

## 4.5 የቅንጅት ስራዎች

### ከፕላን፣በጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ጋር የሚሰሩ ስራዎች

➢ ከአካባቢ ብክለት፣ የካሳ ክፍያ፣ የግድቡ የመስኖ ግንባታ፣

➢ የሚካሄድበት ቦታ፡- አርጆ ዴዴሳ፣ ፊንጫ ስኳር ፋብሪካ/ኩየሳ/

### ከግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ጋር የሚሰሩ ስራዎች

➢ አፋር ክልል የአዋሽ ተፋሰስ ባለሥልጣን ጋር የመስኖና ተፋሰስ ስራዎችን በተመለከተ በጋራ ለማየት

## 4.6 የአፈጻጸም አቅጣጫዎች፣ የክትትልና ድጋፍ ስርዓት

### የአፈጻጸም አቅጣጫዎች

➢ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ስጋትን በመከላከል እንዲሁም የሀገሪቷን ፀጥታ የሚያደፈርሱ አካላትን ለህግ በማቅረብ ሁሉንም ስራዎች በአባላት ሙሉና ንቁ ተሳትፎ የመፈፀም አቅጣጫን መከተል፣

➢ ሁሉንም ዕቅዶች በተቀመጠላቸው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ሳይንጠባጠቡ እንዲፈፀሙ በቼክ-ሊስት መሰረት መመራት፣

- የጋራ ስኬትን መነሻና መድረሻ በማድረግ የብልፅግና ጉዟችን በሁሉም ተግባራት ቅንጅታዊ አሰራርን እና የመናበብ አካሄድን የተከተለ አቅጣጫ መኖሩን ማረጋገጥ፤

**የክትትልና ድጋፍ ስርዓት**

- የቋሚ ኮሚቴውን ተግባራት አፈጻጸም ለመከታተል የሚያግዝ ቼክ-ሊስት መሰረት በማድረግ ወቅታዊ የሥራ ላይ ግምገማዎችን በማድረግ የሚንጠባጠቡ ተግባራት እንዳይኖሩ ክትትል ማድረግ፣
- ቋሚ ኮሚቴዎች በየወሩ የተግባራት አፈፃፀም ግምገማ ማድረግና የየወሩን አፈፃፀም ሪፖርት ለሚመለከታቸው አካላት እንዲልኩ በማድረግ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣

## 4.7 የሚያጋጥሙ ስጋቶችና መፍትሄዎች

**ስጋቶች**

- አንዳንድ አስፈፃሚ መ/ቤቶች ዕቅድ እና ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርታቸውን ወቅቱን ጠብቆ አለመላክ፣
- የቋሚ ኮሚቴው ዋነኛ ተግባር የሆነው የክትትልና ቁጥጥር እንዲሁም የድጋፍ ስራዎች በታቀደ መልኩ ወይም በተያዘላቸው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት አለመከወን፣
- በቂ የሚዲያ ሽፋን በመስክ ምልከታና ከአስፈፃሚ መ/ቤቶች ጋር ለሚደረገው ውይይት ያለማግኘት፣
- ለሚያጋጥሙ ችግሮች በጠንካራ ትግል የመፍታት ውስንነት መኖር ወይም በተገቢው አለመታገል
- በንፁህ መጠጥ ውሃ ዘርፍ፣ በመስኖ ልማት እንዲሁም አካባቢ ጥበቃን መሰረት ያደረጉ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ አለመጠናቀቅ
- በሀገሪቱ የተከሰተው የፀጥታ መደፍረስ፣ የኑሮ መወደድ፣ የዋጋ ግሽበትና የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ የታቀዱ ስራዎችን ለመፈፀም አዳጋች መሆኑ

**መፍትሄዎች**

- አስፈፃሚ መ/ቤቶች የዕቅድና ሪፖርታቸውን እንዲልኩ አስቀድሞ ማሳወቅና ተግባራዊነቱን መከታተል፣

- አባላት በተመደቡበት የቋሚ ኮሚቴው ሥራ ላይ አውቀው እንዲገኙ ማድረግ፣ የተመደቡበትን ኃላፊነት እንዲወጡ የእርስ በራስ የመደጋገፍ ስራ አጠናክሮ መቀጠል፣
- ቋሚ ኮሚቴው ለሚያከናውነው የመስክ ምልከታ ስራ እና ከአስፈፃሚ መ/ቤቶች ጋር የሚደረግ ውይይት ስፋቱንና ከመንግስት የትኩረት አቅጣጫ አንፃር ለህዝብ ግልጽ የሚደረጉ በመሆናቸው የሚዲያ ሽፋን እንዲያገኙ ከም/ቤት ጽ/ቤት ጋር በመነጋገር የሚፈጠሩ ችግሮችን በጋራ ውይይት በመፍታት ለህዝብ ይፋ መደረግ የሚገባቸውን በመለየት በማስፈፀም ይሆናል፣
- ሥራዎቻችንን በነቃ የትግል መንፈስ መምራት፣
- የተጀመሩ የልማት ፕሮጀክቶች ላይ ትኩረት በማድረግ አፈፃፀማቸውን በመስክ ምልከታ በአካል ወርዶ መከታተልና ተጠያቂነት እንዲኖር ማድረግ
- በሀገራችን ለተከሰተው የፀጥታ መደፍረስ ችግር በቀጥታ ተሳታፊ የሆኑ አካላትን ለህግ እንዲቀርቡ መስራትና በኢትዮጵያ የሠላምና የፀጥታ ማስከበር ስራ የሚሰሩ አካላትን በቅንጅት ህረተሰቡን በማሳተፍ የመደገፍ ስራ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ማስቻል፡፡ የኮሮና ቫይረስን ለመከላከል የኮቪድ መመሪያን በመተግበር የጤና ተቋማት የሚያወጡትን የመከላከያ መንገድ ተግባራዊ ማድረግ፡፡

## 5. ማጠቃለያ

የሀገሪቷን የፀጥታ ሁኔታ ትኩረት ባደረገ መልኩ የህብረተሰቡን ችግር ሊፈቱ የሚችሉ በተለይ በንፁህ መጠጥ ውሃ፣ በመስኖ ልማትና በአካባቢ ጥበቃ ላይ የሚሰሩ ፕሮጀክቶች ለተጠቃሚ /ለማህበረሰቡ/ ለማስተላለፍ የሚያስችሉ ተግባራት ይከናወናሉ፡፡

ቋሚ ኮሚቴው ከውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴርና ተጠሪ ተቋማት እንዲሁም የመስኖ ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴርና ተጠሪ ተቋማትን በአጠቃላይ የ6 ተቋማትን የ2014 በጀት ዓመት እቅድና እቅድ አፈፃፀም እየተቀበለ እንዲሁም በመስክ ምልከታ የክትትል ቁጥጥርና ድጋፍ በማድረግ ጥንካሬዎች፣ ድክመቶች፣ ታቅደው ያልተከናወኑና ትኩረት የሚሹ ነጥቦችን የመለየት ስራ በመስራት ለሚመለከተው አካል ሪፖርት የሚያደርግ ይሆናል፡፡

**የውሃ፤መስኖ፤ቆላማ አካባቢ እና የአካባቢ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ**

## በ2014 በጀት ዓመት ጠቅላላ በጀት

| ተ.ቁ. | የበጀት ርዕስ | የበጀት ፍላጐት |
|---|---|---|
| 1 | **የመስክ ምልከታ** | |
| 1.1 | *መደበኛ መስክ* | 941,881.98 |
| 1.2 | *የከተማ መስክ* | 55,000 |
| 1.3 | *ድንገተኛ መስክ* | 55,000 |
| 1.4 | *የቅንጅት መስክ* | 345,000 |
| 2 | **የምክክር መድረክ** | 76,000 |
| 3 | **የመስተንግዶ ወጪ** | 275,000 |
| 4 | **የአላቂ ዕቃ ግዥ** | 641,695 |
| 5 | **ቋሚ ዕቃ ግዥ** | 526,500 |
| | **ጠቅላላ ድምር** | **2,916,076.98** |

# የድርጊት መርሀግብር

| ተ.ቁ | ተግባራት | የሚፈፀሙበት ጊዜ |
|---|---|---|
| 1 | የቋሚ ኮሚቴን ዕቅድ ማዘጋጀት፣ ማጽደቅና ለሚመለከተው መላክ | **እስከ 10/3/2014 ዓ.ም.** |
| 2 | የቋሚ ኮሚቴውን የጊዜ ሰሌዳ የያዘ ቼክሊስት በማዘጋጀት በጋራ መግባባት ማጽደቅና ለሚመለከተው መላክ፣ | **እስከ 13/3/2014 ዓ.ም.** |
| 3 | የአስፈጻሚ ተቋማት የ2ኛ፤የ3ኛ እና 4ኛ ሩብ አፈጻጸም ግምገማ በአባላት፣በንዑስ ኮሚቴና በቋሚ ኮሚቴ በማድረግ፣ ግብረ-መልስ መስጠት | ታህሳስ፣ መጋቢትና ሰኔ/2014ዓ.ም. |
| 4 | የቋሚ ኮሚቴውን የወር፣ የሩብ አመትና አመታዊ የሥራ ሪፖርት ማዘጋጀት፣ መገምገምና መላክ<br>– የየወሩን ከ28-30 ባሉት ቀናት<br>– የየሩብ አመት ወሩ ባለቀ ከ1-5 ባሉት ቀናት ውስጥ<br>– ዓመታዊ የሥራ አፈፃፀም ሪፖርትን ማዘጋጀት መገምገምና ለሚመለከታቸው መላክ | ከታህሳስ - ሰኔ/2014 ዓ.ም (ከዝግጅት እስከ ማጠቃለያ ምዕራፍ) |
| 5 | የሁለቱም ሚኒስቴር መ/ቤት ሥራን መሠረት ያደረገ የአካል ግምገማ መድረክ<br>– የግማሽ ዓመት ግምገማ፡- የውሃ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር<br>– የዓመቱ ማጠቃለያ ግምገማ፡- መስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር | ጥር/2014 ዓ.ም.<br>ሰኔ/2014 ዓ.ም. |
| 6 | የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደርን ፤ አጠቃቀምን እና የተፋሰሶች ልማትን ከባለድርሻ አካላት ጋር የምክክር መድረክ ማዘጋጀት | ታህሳስ 14/2014ዓ.ም |
| | የአከባቢ ጥበቃ እና የአካባቢ ህግ ተከባሪነት ማጎልበት ዙሪያ ከባለድርሻ አካላት ጋር የምክክር መድረክ ማዘጋጀት | ታህሳስ 28/2014ዓ.ም |
| 7 | **የመስክ ምልከታ ማካሄድ**<br>የመጀመሪያ ዙር መደበኛ መስክ ምልከታና ግብረ-መልስ መስጠት | ከህዳር 16-ህዳር 30/2013 ዓ.ም. |
| | የሁለተኛ ዙር መደበኛ መስክ ምልከታና ግብረ-መልስ መስጠት | |
| | የሶስተኛ ዙር መደበኛ መስክ ምልከታና ግብረ-መልስ መስጠት | |
| | አራተኛ ዙር መደበኛ መስክ ምልከታና ግብረ-መልስ መስጠት | |
| | አምስተኛ ዙር መደበኛ መስክ ምልከታና ግብረ-መልስ መስጠት<br>የመጀመሪያ ዙር የቅንጅት መስክ ምልከታና ግብረ-መልስ መስጠት | |
| | የሁለተኛ ዙር የቅንጅት መስክ ምልከታና ግብረ-መልስ መስጠት | |
| | የከተማ የመስክ ምልከታ (የመጀመሪያ ዙርየሁለተኛ እና ዙርየሶስተኛ ዙር) | |
| | ድንገተኛ የመስክ ምልከታ (የመጀመሪያ ዙርየሁለተኛ እና ዙርየሶስተኛ ዙር) | |